# እድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 11 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች የኮሮና ቫይረስ 2019 በሽታን (COVID-19) ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ስላለው የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት 2024-2025 FORMULA) በተመለከተ ለክትባቶቹ ወሳጆች እና ተንከባካቢዎች መረጃ ለመስጠት የቀረበ የክትባት መረጃ ቅጽ

በSARS-CoV-2 ምክንያት የሚመጣውን የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019ን (COVID-19) ለመከላከል ለልጅዎ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (2024-2025 Formula)[1] እየተሰጠው ነው።[2] ይህ የመረጃ መስጫ ቅጽ በአሁኑ ወቅት የCOVID-19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምክንያት ልጅዎ ሊወስደው ስለሚችለው የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (2024-2025 Formula)፣ ከዚህ በኋላ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ተብሎ የሚጠራውን፣ የሚያስከትላቸውን ስጋቶችና የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች በተመለከተ ለመረዳት የሚረዳዎ መረጃ ይዟል። ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት የልጅዎን የክትባት አገልግሎት ሰጪ ያነጋግሩ።

ይህ የመረጃ ቅጽ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል። በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጽ ለማግኘት እባክዎ https://www.covidvaxoption.com/ን ይመልከቱ።

ከዩኤስ የምግብ እና የመድሃኒት አስተዳደር (FDA) የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ (EUA) ሰጥቷል። (ስለ EUA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ "**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ። የ ፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት በአሜሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በ FDA-የተፈቀደለት አይደለም። ስለ ፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት የተመለከተ መረጃ ለማግኘት ይህን የመረጃ ቅጽ ያንብቡ።

## COVID-19 ምንድን ነው?

የCOVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራ የኮሮና ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። በቫይረሱ ከተያዘ ከሌላ ሰው ጋር ንክኪ በማድረግዎ ምክንያት በ COVID-19 ሊያዙ ይችላሉ።

በሽታው በዋናነት ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሊያጠቃ የሚችል የመተንፈሻ አካል ህመም ነው። በCOVID-19 የተያዙ ሰዎች ከመጠነኛ እስከ ለሞት የሚያበቃ ከፍተኛ ህመም የሚደርሱ የተለያዩ ምልክቶች እንደታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል። ምልክቶቹ ለቫይረሱ ከመጋለጥ በኋላ ከ2 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለትን፣ ሳልን፣ የትንፋሽ ማጠርን፣ ድካምን፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ሕመም፣ እራስ ምታት፣ አዲስ የሚፈጠር የጣዕም ወይም ሽታ አለመለየትን፣ የጉሮሮ መሰርሰርን፣ የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛትን፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስን፣ ተቅማጥን ሊይዙ ይችላሉ።

---

[1] የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (2024-2025 Formula) የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ KP.2 የሆነውን SARS- CoV-2 ስፓይክ ፕሮቲንን ያመነጫል።

[2] ልጅዎ የበሽታ መከላከል አቅሙ ዝቅተኛ ከሆነ እና የበሽታ መከላከል አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆነ ግለሰቦች የሚሰጠው ተከታታይ ክትባት በሚሰጥበት ወቅት እድሜያቸው ከ 11 ዓመት ወደ 12 ዓመት እየተቀየረ ከነበረ፣ ለልጅዎ COMIRNATY (COVID-19 ክትባት፣ mRNA) (2024-2025 Formula) (ከዚህ በኋላ COMIRNATYX ተብሎ

የሚጠራው) እየተሰጠ ስለሆነ ይህንን የመረጃ ቅጽ ማግኘት ይችላሉ። COMIRNATY ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች COVID-19ን ለመከላከል በ FDA የተፈቀደለት ክትባት ሲሆን፣ የበሽታ መከላከል አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆነ ግለሰቦች የሚሰጠው ተከታታይ ክትባት በሚሰጥበት ወቅት እድሜያቸው ከ 11 ዓመት ወደ 12 ዓመት እየተቀየረ ለነበረ ሰዎች የክትባቱን የዶዝ መርሃ ግብር እንዲያጠናቅቁ በ EUA ስር የተፈቀደለት ነው። በተፈቀደው የክትባት መርሃ ግብር መሰረት፣ እነዚህ ግለሰቦች እድሜያቸው 12 ዓመት ከመሙላቱ በፊት የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት የሚከተቡ ሲሆን፣ ተከታታዩን የ COMIRNATY ክትባት ግለሰቡ 12 ዓመት ሲሆነው ወይም ከዛ በኋላ ወስደው ይጨርሳሉ። ክትባቱ የሚሰጥበት መርሃ ግብር፥ ዶዝ 1፡ ሳምንት 0፤ ዶዝ 2፥ 3 ሳምንት፤ ዶዝ 3፥ ≥4 ሳምንታት ዶዝ 2 ከተሰጠ በኋላ። በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ ስለፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) COVID-19 ክትባት ስለ ክትባቱ ጥቅማጥቅሞች፣ ጉዳቶች እና የተሰራባቸው ግብዓቶች መረጃን የሚገልጽ ሲሆን፣ ከዚህም ሌላ ክትባቱ ከሚሰጥበት የጊዜ ሰሌዳ እና ክትባቱን ለመጠቀም ከተፈቀደው ዕድሜ በስተቀር ስለልጅዎ የCOMIRNATY አጠቃቀም ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።

## የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ምንድን ነው?

የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት እድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 11 ዓመት የሆኑ ግለሰቦችን ከCOVID-19 ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ክትባት ነው። FDA የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት በ EUA ስር ለአስቸኳይ ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውል ፈቅዷል።

የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ሁሉንም ሰው ላይከላከል ይችላል።

## ልጅዎ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ከመውሰዱ በፊት ለክትባት አቅራቢው መግለጽ ያለብዎ ምንድን ነው?

ለልጅዎ ክትባት አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የልጅዎ የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:

- የትኛውም አለርጂዎች ካለበት
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለበት ከሆነ
- ትኩሳት ካለበት
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለበት
- የበሽታ መከላከል አቅሙ የተዳከመ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከል ስርአት ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰደ ከሆነ
- ነፍሰ ጡር ከሆነች
- የምታጠባ ከሆነ
- ሌላ የCOVID-19 ክትባት ከወሰደ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራሱን ስቶ የሚያውቅ ከሆነ

## ክትባቱ የሚሰጠው እንዴት ነው?

የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት በመርፌ መልኩ በጡንቻ ላይ ይሰጣል።

### <u>እድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት የሆኑ ግለሰቦች</u>

- **ያልተከተቡ ሰዎች**: ሶስት የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ዶዞች ቢያንስ በ11 ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ይሰጣሉ። የመጀመሪያዎቹ 2 ዶዞች በ3 ሳምንታት ልዩነት ይሰጣሉ። ሶስተኛው ዶዝ ሁልተኛው ዶዝ ከተሰጠ ቢያንስ ከ 8 ሳምንታት በኋላ ይሰጣል።
- **ከዚህ ቀደም 1 ዶዝ የበፊቱን የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት የተቀበሉ ግለሰቦች[3]፥** ሁለት የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት ይሰጣቸዋል። የመጀመሪያው የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ዶዝ የበፊቱ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ከተሰጠ ከ3 ሳምንታት በኋላ ሁለተኛ ደግሞ ቢያንስ ከ 8 ሳምንታት በኋላ ይሰጣል።
- **ከዚህ ቀደም 2 ዶዝ ወይም ከዛ በላይ የበፊቱ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት የተቀበሉ ግለሰቦች[3]፥** አንድ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት የሚሰጠው የመጨረሻው የበፊቱ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት ከተሰጠ ከ8 ሳምንታት በኋላ ነው።

[3] የበፊቱ ዶዝ ሲባል ከአሁን በኋላ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት ዶዝን ያመለክታል።

**<u>ዕድሜያቸው ከ 5 እስከ 11 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች</u>**
አንድ ጊዜ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) COVID-19 ክትባት የCOVID-19 ክትባት (2024-2025 Formula) ላልተከተቡ ግለሰቦች ይሰጣል። የማንኛውም የCOVID-19 ክትባት የመጨረሻ ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ቢያንስ 2 ወራት መጠበቅ አለብዎት።

**<u>እድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 11 ዓመት የሆኑ እና የበሽታ መከላከል አቅማቸው የተዳከመ ግለሰቦች</u>**
ተጨማሪ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባቶች ሊሰጡ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።

**የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ማን ማግኘት/መከተብ <u>የለበትም</u>?**
ልጅዎ በሚከተሉት ሁኔታዎች የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት መውሰድ የለበትም፥

- የበፊቱን የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ዶዝ ከወሰደ በኋላ ከባድ አለርጂ ካጋጠመው
- በእነዚህ ክትባቶች በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ አጋጥሞ ከነበረ።

**የዚህ ክትባት ግብአቶች ምንድን ናቸው?**
የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 የሚከተሉትን ግብአቶች ይይዛል፡ ሜሴንጀር ሪቦኑክለይክ አሲድ (mRNA)፣ ሊፒዶች ((4-ሀይድሮክሲቡቲል)አዛንዲል)bis(hexane-6,1-diyl)bis(2-hexyldecanoate)፣ 2 [(ፖሊትሊን ግሎኮል)-2000]-N,N-ዳይትሬድሲላሴታሚድ፣ 1,2-ዲስትሮይልl-sn-ግሊሴሮ-3- ፎስፎኮሊን እና ኮሌስትሮል)፣ ትሮሜታሚን፣ ትሮሜታሚን ሃይድሮክሎራይድ፣ እና ሱክሮስ። ከዚህም ሌላ ዕድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት ለሆኑ ሰዎች ጥቅም ላይ እንዲውል የተዘጋጀው የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ሶዲየም ክሎራይድ ይይዛል።

**ይህ ክትባት ከዚህ ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ውሏል?**
በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዕድሜያቸው 6 ወራት እና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች በ EUA ስር የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ወስደዋል።

በህክምና ሙከራዎች ወደ 1,200 የሚጠጉ ዕድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 23 ወር የሆኑ ሰዎች፣ ወደ 1,800 የሚጠጉ ዕድሜያቸው ከ 2 ዓመት እስከ 4 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ ወደ 3,100 የሚጠጉ ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት እስከ 11 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባትን ቢያንስ 1 ዶዝ ወስደዋል (ዋናው ሞኖቫለንት/monovalent[4])። በሌሎች ክሊኒካል ሙከራዎች ደግሞ፣ ወደ 23,000 የሚጠጉ እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ቢያንስ 1 የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) ዶዝ ወስደዋል (ዋናው ሞኖቫለንት/monovalent)።

በህክምና ሙከራዎች 60 ዕድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ 113 ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት እስከ 11 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ 107 ዕድሜያቸው ከ 12 ዓመት እስከ 17 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ 103 ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት እስከ 55 ዓመት የሆኑ ሰዎች፣ 106 ዕድሜያቸው ከ 55 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech)፣ ባይቫለንትን (Bivalent) አንድ ዶዝ ወስደዋል።[5]

---

[4] የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (በፊት ሞኖቫለንት/Monovalent ተብሎ የሚታወቀው)

የኦሪጂናል SARS-CoV-2ን ብቻ ስፓይክ ፕሮቲንን የሚያመነጭ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ይገልጻል። ይህ ክትባት በአሁኑ ሰዓት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል አልተፈቀደለትም።

[5] የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) የኦሪጂናል SARS-CoV-2ን እና ኦሚክሮን (Omicron) BA.4/BA.5 SARS-CoV-2 ስፓይክ ፕሮቲንን የሚያመነጭ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ይገልጻል። ይህ ክትባት በአሁኑ ሰዓት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል አልተፈቀደለትም።

## የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

FDA የCOVID-19 በሽታ ለመከላከል የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት ጥቅም ላይ እንዲውል ፈቅዷል።

የክትባቱ ከCOVID-19 መከላከል የቆይታ ጊዜ በአሁኑ ወቅት አልታወቀም።

## የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የ COVID-19 ክትባት የሚያስከትላቸው ስጋቶች ምንድን ናቸው?

ክትባቱ ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት አጋጣሚ በጣም ጥቂት ነው። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው አንድ ዶዝ ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ዲቃዎች ጀምሮ እስከ አንድ ሰአት ያክል ነው። በዚህም ምክንያት የክትባት አቅራቢው የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ልጅዎ ክትባቱን በወሰደበት ቦታ እንዲቆይ ሊጠይቀው ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡

- የመተንፈስ ችግር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- ከባድ የሙሉ ሰውነት መንደብደብ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) እና ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት የmRNA የCOVID-19 ክትባት በወሰዱ ሰዎች ላይ ተከስቷል። የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ተከትሎ ማዮካርዲቲስ እና ፔሪካርዲቲስ በብዛት የተከሰቱት እድሜያቸው ከ12 ዓመት እስከ 17 ዓመት በሆኑ ወንዶች ላይ ነው። በእነዚህ አብዛኞቹ ግለሰቦች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት ክትባቱን በወሰዱ በጥቂት ናት ውስጥ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ልጅዎ ክትባቱን ከወሰደ በኋላ፣ በተለይም የክትባቱን ዶዝ ከወሰደ በኋላ ባሉት 2 ሳምንታት ውስጥ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩበት ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፡

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር ወይም የመተንፈስ ችግር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት

ተጨማሪ ምልክቶች፣ በተለይም በልጆች ላይ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፥

- እራስን መሳት
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ብስጩነት
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ዝቅተኛ የሆነ አመጋገብ
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ድካም እና የአቅም ማነስ
- የማያቋርጥ ማስመለስ
- የማያቋርጥ የሆድ ህመም
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ቀዝቃዛ የሆነ የገረጣ ቆዳ

ከየፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ጋር ሪፖርት የተደረጉት የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ከባድ አለርጂ
- እንደ መንደብደብ፣ ማሳከክ፣ ሽፍታ ወይም የፊት እብጠት የመሳሰሉ ከባድ ያልሆኑ አለርጂዎች
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር ህመም/መቆጣት

- ድካም
- የራስ ምታት
- የጡንቻ ህመም
- ብርድ ብርድ ማለት
- የመገጣጠሚያ ህመም
- ትኩሳት
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር እብጠት
- ክትባቱ በተወጋበት ቦታ የሚፈጠር የሰውነት መቅላት
- ማቅለሽለሽ
- ጥሩ ያልሆነ ስሜት
- የብሽሽት እብጠት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- ተቅማጥ
- ማስመለስ
- የእጅ ህመም
- ከክትባቱ ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው ያውቁ ከሆነ
- መፍዘዝ
- ብስጩነት
- ትኩሳት በሚኖር ጊዜ የሚፈጠር ማንቀጥቀጥ

ክትባቱ የሚያስከትላቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች እነዚህ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። ከባድና ያልተጠበቁ የጎኒዮሽ ውጤቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ክትባቱ ሊያስከትላቸው የሚችላቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች አሁንም በመጠናት ናቸው።

**የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠሙኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ልጅዎ ከባድ አለርጂ ካጋጠመው ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል ይሂዱ።

የትኛውም ልጅዎን የሚያሳስብ ወይም የማይጠፉ የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠመው ለክትባት አቅራቢው ወይም ለልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይደውሉ።

የክትባቱን የጎኒዮሽ ውጤቶች ለFDA/CDC የክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ሲስተም (VAERS) ሪፖርት ያድርጉ። የVAERS የነጻ ጥሪ መስመር 1-800-822-7967 ነው ወይም በኦንላይን በ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ። እባክዎ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ በሳጥን #18 ስር በሚገኘው የመጀመሪያው መስመር ላይ “የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት (2024-2025 Formula) EUA” የሚለውን ያካቱ።

ከዚህ በተጨማሪም የጎኒዮሽ ውጤቶችን ለPfizer Inc. ከዚህ በታች በተገለጸው የግንኙነት መረጃ ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ።

| ድረ ገጽ | የፋክስ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| www.pfizersafetyreporting.com | 1-866-635-8337 | 1-800-438-1985 |

**የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ልጁ እንዳይወስድ ብወስን ምን ይሆናል?**
በ EUA ስር፣ ይህንን ክትባት ለመውሰድ ለመስማማት ወይም ለመቃወም የቀረበ አማራጭ አለ። ክትባቱን ልጅዎ እንዳይወስድ ቢወስኑ፣ በመደበኛ የህክምና እንክብካቤ ደረጃ ላይ ለውጥ አይፈጥርም።

**ከፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ሌላ COVID-19ን የሚከላከሉ ክትባቶች አሉ?**
በ EUA ስር የ SARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ KP.2 ስፓይክ ፕሮቲን የሚያመነጩ ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች COVID-19ን የሚከላከሉ ክትባቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

**ልጁ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ መውሰድ ይችላል?**
ለልጅዎ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባትን ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ ስለመውሰድ እያሰቡ ከሆነ፣ በአማራጮቹ ላይ ከልጅዎ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይወያዩ።

**የልጁ በሽታ መከላከል አቅም የተዳከመ ከሆነ ምን ይሆናል?**
የበሽታ መከላከል አቅማቸው የተዳከመ እና ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 11 ዓመት የሆኑ ግለሰቦች ተጨማሪ የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት ዶዝ ሊወስዱ ይችላሉ (ከላይ **ክትባቱ የሚሰጠው እንዴት ነው?** የሚለውን ይመልከቱ)።

ክትባቶቹ የበሽታ መከላከል አቅማቸው ለተዳመ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከCOVID-19 ላይከላከሉ ስለሚችሉ፣ ልጅዎ COVID-19ን ለመከላከል እንዲረዳው አካላዊ ጥንቃቄዎችን መከተሉን መቀጠል አለበት። ከልጅዎ ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ መከተብ አለባቸው።

**ነፍሰ ጡርነትን ወይም ማጥባትን በተመለከተ ያለው መረጃስ ምንድን ነው?**
ልጅዎ ነፍሰ ጡር ከሆነች ወይም የምታጠባ ከሆነች፣ ስላሉት አማራጮች ከልጅዎ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይወያዩ።

**ይህ ክትባት ለልጁ COVID-19 ሊያስይዘው ይችላል?**
አያሲዝም። ይህ ክትባት SARS-Cov-2ን የማይዝ በመሆኑ ልጅዎን በCOVID-19 አያስይዝም።

**ተጨማሪ መረጃ**
ጥያቄዎች ካሉዎ ከዚህ በታች የተገለጸውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም ከታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር ይደውሉ። በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጾችን ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች የቀረበውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ።

| አለም አቀፍ ድረገጽ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|
| www.cvdvaccine.com | 1-877-829-2619<br>(1-877-VAX-CO19) |

**ተጨማሪ መረጃ እንዴት አገኛለሁ?**

- የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ።
- CDCን በ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html ይጎብኙ።
- FDAን በ https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm-legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization ላይ ይጎብኙ።
- የአካባቢዎን ወይም የግዛትዎን የማህበረሰብ ጤና መምሪያ ያነጋግሩ።

**የክትባት መረጃ የት ይመዘገባል?**

ክትባት አቅራቢው የልጅዎን የክትባት መረጃ በግዛት/አካባቢ የክትባት መረጃ ሲስተም (IIS) ወይም ሌላ የተመደበ ሲስተም ላይ ሊያካትት ይችላል። ስለ IISዎች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.htmlን ይጎብኙ።

**የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም ምንድን ነው?**

የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም (CICP) ይህን ክትባት ጨምሮ በተወሰኑ መድሀኒቶች ወይም ክትባቶች የተነሳ ከባድ ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች የሚከፍሏቸው የህክምና እንክብካቤ ወጪዎች እና ሌሎች ልዩ ወጪዎች እንዲከፈሏቸው የሚያግዝ የፌደራል ፕሮግራም ነው። በጠቅላላው የካሳ ጥያቄው ክትባቱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) አመት ውስጥ ለCICP መቅረብ አለበት። ስለዚህ ፕሮግራም የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.hrsa.gov/cicp/ን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-855-266-2427 ይደውሉ።

**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**

FDA የፋይዘር ባዮቴክ (Pfizer-BioNTech) የCOVID-19 ክትባት EUA ተብሎ በሚጠራው የአስቸኳይ ጊዜ አቅርቦት አሰራር ስር እንዲሰጥ አድርጓል። EUA በCOVID-19 ወረርሽኝ ቆይታ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ መድሀኒቶችን እና የባዮሎጂካል ምርቶችን ለመጠቀም አሳማኝ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ይህን በሚፈቅደው የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (HHS) መግለጫ ድጋፍ አግኝቷል። በአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ የተሰጠው ምርት ከ FDA ፍቃድ ካገኘ ምርት ጋር በ FDA አንድ አይነት የግምገማ ሂደት አይደረግለትም።

FDA የተወሰኑ መስፈርቶች ሲሟሉ EUA ሊሰጥ የሚችል ሲሆን መስፈርቶቹ በቂ፣ የተፈቀዱ፣ ዝግጁ አማራጮች አለመገኘትን ይይዛሉ። በተጨማሪም የFDA ውሳኔ በሚቀርቡለት ምርቱ በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ወቅት COVID-19ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል እና የምርቱ የታወቁና ሊሰሩ የሚችሉ ጥቅሞችን እና ከምርቱ የታወቁና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ይልቅ ጥቅሞቹ እንደሚያመዝኑ በሚያሳዩ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሰረታል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ምርቱ በ EUA ስር ጥቅም ላይ እንዲውል እነዚህ ሁሉ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው።

ካልተቋረጠ ወይም ካልተሻረ በስተቀር (ይህ ከሆነ ግን፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ምርቱ በ EUA ስር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም)፣ የ ኮቪድ-19 የ EUA አስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ አስፈላጊነት እስካለ ድረስ፣ የዚህ ምርት EUA ተግባራዊ እንደሆነ የሚቆይ ይሆናል።

BIONTECH

የተመረተው ለ፥
BioNTech Manufacturing GmbH
An der Goldgrube 12
55131 Mainz, Germany

Pfizer

አምራች፥
Pfizer Inc., New York, NY 10001
LAB-1572-3.5c
የተሻሻለበት ቀን: 22 ነሃሴ 2024

GDTI: 0886983000585